# ይ ቻ ላ ል !

**መቻል አለበት!** **መቻል ይኖርበታል!**

# YICHALAL!

ቅጽ ፩፣ ቁጥር ፩ ግንቦት ፯ ቀን ፪ሺህ ፩ ዓ/ም.

በኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት የሕዝብ ግንኙነትና ማስታወቂያ ክፍል በየወሩ የሚወጣ ልሳን


UEDF, P.O.Box 73796* Washington D.C.20056-3796; hebret.org


## ርዕሰ-አንቀጽ፡

## በሕዝባዊ ትግል ሕዝባዊ ድልን ማረጋገጥ ይቻላል፤ አ ዎ ን ይ ቻ ላ ል!

ከአራት ዓመታት በፊት የኢትዮጵያ ሕዝብ ለመብቶቹ መከበር ያካሄደውን የረጅም ጊዜ መራር ትግል በድል የተወጣበትና የአምባ-ገነን ሥርዓቶችን አዙሪት ሰብሮ፣ አይበገሬነቱን፣ አንድነቱን፣ ብስለቱንና ታላቅነቱን ያበሰረበት ዳግም አድዋን ያስመሰከረበትን ግንቦት ሰባት ዛሬ የምንዘክረው ለነዚያ የግንቦት ድሎች እውን መሆን ጊዜአቸውን፣ ጉልበታቸውን፣ ጥሪታቸውን፣ ንብረታቸውን፣ አጠቃላይ ሥራቸውን፣ ትዳራቸውን፣ ቤተሰባቸውን፣ ደማቸውንና ምትክ የሌለውን ውድ ሕይዎታቸውን ጭምር መስዋዕት ያደረጉ ሥፍር-ቁጥር የሌላቸውን ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችንን ከልብ በማሰብና አድናቆታችንንና አክብሮታችንን በመግለጽ ነው፡፡ በዚች ቀን ለአገር አንድነትና ለሕዝብ ሁለንተናዊ መብቶች መከበር በልዩ ልዩ መልክ ግንባር-ቀደም ፍልሚያ ያደረጉና አሁንም እያደረጉ ያሉ ታጋዮች፣ እንዲሁም በግንቦት ድሎች መቀልበስ ሳቢያ ቂም-በቀል በቋጠሩ የሕወሓት/ኢሕአዴግ ቁንጮዎች ታፍኖና ተረግጦ ስቃዩን እያየ ላለው ሕዝባችን የምናረጋግጠው ሃቅ የግንቦት የሕዝብ ድሎች ዳግም እውን እንደሚሆኑና መስዋዕትነታቸው ከንቱ እንደማይቀር ነው፡፡

እንደ ኢትዮጵያ ላለ የረጅም ዘመን ታሪክ ላልት አገርም እንኳ ቢሆን አራት ዓመታት፣ በተለይም የስቃይና የአፈና ዓመታት፣ በጣም ብዙ ጊዜ ነው፡፡ እነዚኽ አራት ዓመታት የሕዝብ ድል የተቀለበሰበት፣ ገዥው ክፍል ምን ጊዜም የሚፈራው የሕዝብ አንድነትን ስለሆነ ሕዝባችን ዳግም በአንድነቱ አንድነቱንና መብቶቹን እንዳያስከብር ከጊዜ ወደ ጊዜ የአፈና መረቦቹን እያጠበቀና እያጧጧፈ ያለበት፣ "ሕጋዊ" ሆነው ለሚንቀሳቀሱ ድርጅቶች ሳይቀር የፖለቲካ ምኅዳሩ ይበልጥ እየጠበበ የመጣበት፣ ሕዝባችን ታይቶ ተሰምቶ ለማይታወቅ ዙሪያ ጥምጥም ችግሮች ተዳርጎ የሚገኝበት፣ የአገራችን አንጡራ መሬቶች ለባዕዳን አሳልፎ የተሰጠበት፣ መሠረታዊ የሆኑ የኤኮኖሚ፣ የፖለቲካና የማኅበራዊ ችግሮቻችን ይበልጥ ሥር እየሰደዱ፣ የፖለቲካ ውጥረቶች ይበልጥ እየተካረሩ የሄዱበት፣ የአገራችን አንድነት በውጭም ሆነ በውስጥ ለከፍተኛ አደጋ የተጋለጠበት፣ በአንፃሩ

በተቃዋሚው ጎራ የቆመው ክፍል መተካላዊ የሆነ የትግል አንድነት መዳረሻው የተሳከረበትና አቅጣጫው የዋለለበት ፈታኝ ዓመታት መሆናቸው ግልፅ ነው።

በታሪክ አጋጣሚ ከምንገኝበት አዘቅት ለመውጣት አቅምና ፍላጎቱ፣ ችሎታና ብቃቱ በዚኽም ትውልድ አለና ከግልና ከድርጅት ጥቅም ይበልጥ አገራችንንና ሕዝባችንን አስቀድመን፣ በሚያለያዩት ነጥቦች ሣይሆን በሚያግባቡ የጋራ ቁም-ነገሮች ላይ አተኩረን፣ ለሰከነ ትግል ተዘጋጅተን፣ ብሔራዊ እርቅን፣ ሰላምና አንድነትን በራሳችን አረጋግጠን፣ ቁርጠኝነትን ሰንቀን  ከተነሣን አስተማማኝ ሕዝባዊ ድልን መቀዳጀት ይቻላል። ተሸብሮ ለማሸበር በሚከጅል፣ ፈርቶ ለማስፈራት በሚኳትን፣ ተጨንቆ ለማስጨነቅ በሚጥር፣ አልፎም አጥፍቶ ለመጥፋት በሚጓዝ፣ በአጉል እልህና እብሪት በተወጠረ የጥፋት ቡድን መዳፍ ውስጥ የወደቀች አገራችንንና ለሽብር ዱላው ሰለባ የሆነውን ሕዝባችንን ከቀጣይ ስቃይ ማላቀቅ የሚቻለው በጊዚያዊ የፖለቲካ ዋጋ ወይም 'የጠላቴ ጠላት' በሚል አጉል ፈሊጥ ሣይሆን አሁንም በአገር አንድነትና በሕዝብ ሉዓላዊነት መርኅ ላይ ከተመሠረተ የትግል ትብብርና ትሥሥር በሚፈልቅ የግብ-ፈር (ስትራቴጂ) ብቻ ነው።

ዘለቄታዊነት ያለው አዎንታዊ ውጤት እንዲገኝ ጊዜው ሲደርስ ከሚደረግ ከቡድንና ከድርጅት ጠባብ አስተሳሰብ ተላቅቀን ከትንንሽ እይታዎች ተወግደን፣ የዛሬውን ሣይሆን የነገውን ጭምር ባመዛዘነ መልኩ አገርና ሕዝብን ባስቀደመ ቁርጠኝነት የጋራ ትግሉ እንዲጎለብት በማሰብ ነው ኅብረታችን ቅድመ-ምርጫ ዘጠና-ሰባትም ይሁን በኋላ ሳይታክት አበክሮ የሚወተውተው። ለዚኽም ምርጫ ሲባል በጋራ፣ ድርድር ሲባል ከሕዝብ ተደብቆ ሣይሆን በይፋና በጋራ፣ የሕዝብ ድምፅ በጠራራ ፀሐይ ሲሰረቅ የለም አንድ ላይ ቆመን እናስከብር በማለት ቅልበሣው ሥር ሳይሰድ የጋራ ምክክር እንዲደረግ ለመስከረም ሃያና ሃያ-አንድ ዘጠና ስምንት አዲስ አበባ ላይ *"የሰላም፣ የዜጎች አንድነት ትስስርና የዴሞክራሲ አገር-አቀፍ ጉባዔ"* እንዲጠራ ይኽንንም በመደገፍ መስከረም ሃያ-ሁለት በዋና ዋና ከተሞችና በውጭ አገርም ጉባዔው ለሚደርስበት ውጤት በጉባዔው ስም *የድጋፍ ሰልፍ* እንዲደረግ፣ ይኽም በአገዛዙ እክልና በልዩ ልዩ ድክመቶች ምክንያት ሳይሣካ ሲቀር ለሦስት ቀን ቤት ውስጥ የመዋል እርምጃ እንዲወሰድና ቀጣይ እርምጃዎችን በማዘጋጀት፣ ከዚያም ከድርጅት መሪዎች ጀምሮ እልፍ አእላፍ ታጋዮች በግፍ ሲታሠሩ ይኽ የዚኽ ድርጅት የዚያ ድርጅት የሚያሰኝ ሣይሆን ጉዳዩ አጠቃላይ የኢትዮጵያ ሕዝብ ጉዳይ ስለሆነ የጋራ የሆነ *"የቀውጢ ጊዜ ግብረ-ኃይል"* እንዲቋቋምና ሰላማዊ ሰልፍም ይሁን ዲፕሎማሲያዊ ዘመቻዎችን እንዲሁም ሌሎች እንቅሳቄዎችን <u>በጋራ</u> እንድናደርግ፣ የቅንጅት መሪዎች ከተፈቱም በኋላ የተቃዋሚው ጎራ እራሱን መርምሮ በአዲስ መንፈስና መልክ እንዲሸጋሸግና እንዲሰባሰብ፣ ወዘተ... ጥረት ሲያደርግ የቆየው። በጋራ ትግል ላይ ያለው እምነት በአባባል ደረጃ ብቻ የሚቆም አለመሆኑንና ቁርጠኝነቱን በተግባር ለመግለጽ የውስጥ አደረጃጀቱን ውደ ጥምረት በማሳደግ ትግሉን በተሻለ ትኩረት በማካሄድ ላይ ይገኛል።

ለአገርና ለሕዝብ የመታደጊያ ጊዜው ዛሬ ነው። በተናጠል በሚደረግ ጥረት ሊባክን የሚገባው አቅምና ጉልበት ሊኖር አያስፈልግም። በኛ በኩል አሁንም የምንለው 'በጋራ ትግል አስተማማኝ ድል' ነውና፣ በመርኅ ላይ የተመሠረተ የትግል አንድነት በመመሥረት ሕዝባችንን መልሰን የትግሉ ባለቤትና ማዕከል ካደረግን ቅልበሳውን ቀልብሰን የግንቦት የሕዝብ ድሎችን ዳግም እውን ማድረግ እንችላለን፣ በዚኽም የአንድነት እርምጃ የሕዝባችንን መብቶች ማስከበርና የአገራችንን አንድነት ማስጠበቅ ይቻላል! መቻልም አለበት! መቻልም ይኖርበታል! እንላለን። ለዚኽም የድርጅታችንን (የኅብረታችንን) ልሳን እነሆ <u>"ይቻላል!"</u> ብለን ሰይመነዋል። አዎን ይቻላል! መቻል አለበት!

እንበርታ!
አስተማማኝ ድል በጋራ ትግል!!

*ይቻላል! ቅጽ ፩፣ ቁጥር ፩፣ ግንቦት ፯ ቀን ፪ ሺህ ፩ ዓ/ም.*

## ሐተታ፤

## በእርግጥ ይቻላል፣ መቻልም አለበት፣ መቻልም ይኖርበታል!

የኢትዮጵያ ዴሞክራቶች የኢሕአዴግን ሥርዓትና የግንቦትን የሕዝብ ድሎች ቅልበሳ በቁርጠኝነት ለመታገልና የሚጠበቀውን መስዋእትነት ለመክፈል ፈቃዱም ውሳኔውም ሳያንሳቸው ለዚኽ ታሪካዊ ተልዕኮ የሚመጥን የጋራ ስትራቴጂ ቀይሰው የመንቀሳቀስ ችግር እንዳለባቸው ማንም አሌ ሊለው የማይችል ሃቅ ነው:: ይኽ የሆነበት ምክንያት ከግንቦት ቅልበሳ ወዲኽ በአገራችን ቁልፍ የሆኑ የፖለቲካ ጥያቄዎች ዙሪያ ስምምነት በአለመኖሩ አይደለም:: በበርካታ ቁም ነገሮች በተለይም ደግሞ የተያዘው ቅልበሳ የማይቆም የጥፋት ሂደት እንደሆነ፣ ይኽንን ሂደት ለመቀልበስ ሕዝቡን ማዕከል ያደረገ ተጋድሎ እንደሚያስፈልግና ይኽ ካልሆነ ደግሞ ቅልበሳው አገራችን በረጅም ጊዜ ታሪኳ አይታም ሰምታም በማታውቀው መልክ ጎልውናዋን ፈተና ላይ የሚጥል መዘዝ ይኖረዋል በሚሉት ጥያቄዎች ላይ "በደፈናው" ሊባሉ የሚችሉ ስምምነቶች አሉ:: ሆኖም ከነዚህ ተነስተን በተጨባጭ ለሁኔታው የሚመጥን የትግል ስትራቴጂ ለማውጣት ወደ ዝርዝር ስንገባ ከባድ ከባድ የሆኑ የእይታና የትንተና ልዩነቶች ስለሚንፀባረቁ ለዚች አገራችን ያለንን ህልምና ራእይ ተግባራዊ እንዳናደርግ አንቀው የያዙን ይመስለናል::

አንደኛ የተያዘው ቅልበሳ አሳሳቢና የኢሕአዴግ መሪዎች ከያዙት ሥልጣን በሕዝብ ተገድደው ከመውረድና ከአፋኝ ሥርዓታቸው መወገድ በመለስ ሊገታ የማይችል እንደሆነና ይኽ ግፈኛ ሥርዓት እስከቀጠለ ድረስ ደግሞ የምንመኘውና የምንታገልለት ዴሞክራሲያዊ ሕገ-መንግሥታዊ ሥርዓት ቀርቶ ከግንቦት በፊት በጭላንጭል የነበሩና ዛሬ ደብዛቸው የጠፋው መብቶች እንደገና እውን የሚሆኑበት ምንም ተአምር እንደማይኖር ሃቀኛ ዴሞክራቶችና አገር-ወዳድ ኃይሎች ብቻ ሣይሆኑ ሕዝባችን ከዳር-እስከ-ዳር የሚስማማበት ሃቅ ነው:: ሆኖም በዚኽ "ቀጣይነት" ጉዳይ ስምምነት ያለውን ያኽል የቅልበሳው ሂደት ዋና ዋና ገፅታዎች እየተቀያየሩ እንደሚሄዱና ከዚኽ ተለዋዋጭ ሁኔታ ጋር ትኩረታችንንና የትግል መፈክሮቻችንን ለሁኔታው እንደሚመጥኑ አድርጎ ማስተካከል እንደሚያስፈልግ በቂና የጋራ የሆነ ግንዛቤ ያለ አይመስለንም::

ቅልበሳው ገና በአፍላ ደረጃ የነበረባቸው የግንቦት ማግስት ወራት የኢሕአዴግ መሪዎች በግልፅ፣ በይፋና በጅምላ በሽብር ጎዳና የተሰማሩባቸው ወራት ነበሩ:: በመሆኑም በወቅቱ በዚኽ በቅልበሳው የአጠቃላይ አፈናና ቀውጢ የፖለቲካ ገፅታ ላይ አተኩረን የታሰሩት ይፈቱ፣ ለሕዝብ ድምፅ መከበር ምትክ የሌለውን ውድ ሕይዎታቸውን መስዋዕት ላደረጉ ዜጎች ተጠያቂነት ይኑር፣ ወዘተ... እያልን ለዴሞክራሲ፣ ለሕግ የበላይነት፣ ለዳኝነት ነፃነት፣ ለነፃው ፕረስ ጎልውናና ይኽንን ሁሉ ደግሞ "የሕዝብ ድምፅ ይከበር" በሚል መፈክራችን ጠቅለል አድርገን አቅርበን ክቡር የሆነ መስዋዕትነት የተከፈለበት ትግል አካሂደናል። ዛሬ የተያዘው ቅልበሳ በአገር ውስጥም ሆነ በዓለም-አቀፍ ደረጃም ዓይንና ቀልብ በሚስብ የጅምላ አፈናና የሽብር ገፅታው ጎልቶ የሚታይበት ወቅት ውስጥ አይደለንም:: በየካቲት ቅልበሳ ማግስትም ቢሆን ቀይ-ሽብር ለዓመታት አልቀጠለም:: ይኽ ግን የቅልበሳውን መደርጀትና መደራጀት ብሎም አገራችን የሰማይ ስባሪ የሚያክሉ ዙሪያ ጥምጥም የቀውስ አዙሪቶች ውስጥ መግባቷን እንጂ ለሕዝባችን የእፎይታ ዘመን የሚያበስር አልነበረም::

ዛሬም ከዚኽ የተለየ ሁኔታ አይኖርም:: በኛ በኩል ገና ከጧቱ ነበር የቅልበሳውን መዘዝ አደገኛነት የወተወትነው:: ቅልበሳው እየየደረጀና እየተደራጀ ሲሄድ በሰኔ ፺፯ እና በጥቅምት ፺፰ የተከሰተው ጅምላ አፈሳና ጅምላ ግድያ ነጋ ጠባ "አላስፈላጊ" ሆነው ጋብ የሚሉበት

ሁኔታ አለ፡፡ ይኸ ማለት ግን በየጊዜው እነሱው የሚያስጨብጡንን አጀንዳ እያነገብን በአልሆነ አቅጣጫ እንድንባዝንና ከሁሉም በላይ ደግሞ በኅብረተሰቡ ውስጥ ለመንዛት የሚሞክሩት የመሸበር መንፈስ "ሳይረግብ" እንዲቀጥል ወከባውና አፈናው በመሪዎች፣ በግለሰቦች፣ በግንቦቱ ሳቢያ ከቂመኞቹ የመንግሥት መሪዎችና የመንደር ካድሬዎች ዓይን ውስጥ የገቡ ገበሬዎች፣ ሠራተኞች፣ ወጣቶች፣ ምሁራን፣ ነጋዴዎች፣ ታክሲ ነጅዎች፣ ወዘተ... ላይ የአፈናውና የወከባው ሂደት ይቆማል ማለት እንዳልሆነ ግልፅ ነው፡፡ ዛሬ በዓይናችን ሥር የምናየውም እውነታ ይኸው ነው፡፡ በቀጣዩም ጊዜ ከዚኸ የተለየ ሁኔታ አይኖርም፡፡

ይኸ እንዳለ ሆኖ በመጭው ጊዜ ቅልበሳው ከዚኸ የአፈናና የሽብር ፖለቲካዊ ሊባል የሚችል ገፅታው በተጨማሪ በማይናቅ "የአማራጭ ዝርፊያ" ገፅታው እየጎላ እንደሚሄድ ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው፡፡ በምርጫው ዘመቻ ወቅት ተቃዋሚ ኃይሎች በተለይም ኅብረቱና ቅንጅቱ የኢሕአዴግን የኢኮኖሚና የማኅበራዊ ፖሊሲዎች "አገር አውዳሚ" ብለው በሕዝብ ፊት አጋልጠው ታግለዋቸዋል፡፡ አያይዘውም የምንገኝበት የረሃብና የድህነት አዙሪት ተሰብሮ ከድህነት የመላቀቂያና የብልጽግና ጎዳና ያስይዙናል ያሏቸውን አማራጭ ፖሊሲዎች አቅርበው ሕዝባችንን ቀስቅሰው ነበር፡፡ ዛሬ ኢሕአዴግ የሕዝብ ድምፅ ሰርቆ ሥልጣን ላይ ሙጥኝ ብየ እቀጥላለሁ ሲል ይኸ የሽፍጥ አካሄድ ሌላ ትርጉም የለውም፡፡ ለገበሬው፣ ለወጣቱ ሥራ-አጥ፣ ለሠራተኛው፣ ለነጋዴው ለብሔራዊ ጥሪት-አፍሳሹ (ኢንቬስተሩ)፣ ወዘተ... ቀርበው የነበሩት በጎና ሕዝባዊ አማራጮች ቀርተው እኛም ያወገዝናቸው፣ ሕዝባችንም በድምፁ አክ-እንትፍ ብሎ የሻራቸው የጥፋት ፖሊሲዎች ይቀጥላሉ ማለት ነው፡፡ ይኸ ሲሆን ደግሞ በቀጣዩ ጊዜ ሽዎችንና ብዙ አስርተ-ሽዎችን ከሚዳስሰው የፖለቲካ አፈና ይልቅ እየጎላ የሚሄደው የሚሊዮኖችን ኅልውና የሚፈታተነው የኢኮኖሚ፣ የማኅበራዊና የሞራል ቀውስ እንደሚሆን ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው፡፡ በዚኸ ላይ የኢሕአዴግ ሽብርና በተቃዋሚዎች ጎራ በተጠናወተንና  በሚታየው መዝረክረክ ሳቢያ የሚከሰተው የአመራር ክፍተት ሲደማመሩ በኅብረተሰባችን ውስጥ አስከፊ የሆነ ጨለምተኝነትና የትጥቅ መፍታት አባዜ እንደሚሰፍን መጠራጠር የሚቻል አይመስለንም፡፡ የጋራ ትግል ስትራቴጂያችንን ስንነድፍ ይኸንን የቅልበሳው ዋና ዋና ገፅታዎች የመቀያየር ሂደት ልብ ካላልንና ፖለቲካ ገፅታው ላይ ብቻ አተኩረን እነዚኸን ከጊዜ ጋር እየጎለበቱ የሚሄዱ የቅልበሳ ማግስት መዘዞች ከስሌት ካላስገባን ቀጣዩ ትግል ከሕዝብ አንፃር እየተንሳፈፈና የትም የማያደርስ የሚሆንበት አደጋ አለ፡፡ ይኸ ደግሞ ወደ ሁለተኛው የደፈና ስምምነትና የተቸባጭ አካሄድ ልዩነት ነጥብ ያመጣናል፡፡

በሃቀኛ አገር-ወዳዶችና ዴሞክራቶች ጎራ የኢሕአዴግ መሪዎች ከጦር የሚፈሩትንና ብርክ የሚያስይዛቸውን ሕዝባዊ ተሳትፎና ትግል መልሶ የመቀስቀሱና በአንድ አቅጣጫ እንዲገፉ የማድረጉ ጉዳይ ከልብ የምናምንበት የሕዝባዊና ሰላማዊ ትግላችን ስትራቴጂ የማዕዘን ድንጋይ ሆኖ ይታያል፡፡ ሆኖም የግንቦትን ድሎች ማስከበርን ያኸል ክቡር ዓላማ አንግቦ የሚካሄደው ትግላችን የኅብረተሰቡን ተጨባጭ ጭንቀቶች ስሌት ውስጥ ባለማስገባቱ የተነሳ "ሕዝባችንን ከዳር-እስከ-ዳር እንቀሳቅሰን" ለሚለው የተቀደሰና በጎ አገራዊ ምኞታችን የሚመጥን ስትራቴጂ እንዳንቀይስ አድርጎናል፡፡ ሚሊዮኖችን ወደ ትግሉ ለመመለስ የምንከተለው ስትራቴጂ ከዚኸ የቅልበሳው ዋና ገፅታ እየሆነ ከመጣውና ከሚቀጥለው አማራጭ ዝርፊያና ይኸም በኅብረተሰባችን ውስጥ በተጨባጭ ከሚያስከትለው ጨለምተኝነትና ከባድ የኅልውና ቀውስ አንፃር ሳይሆን የግንቦትን ቅልበሳ በሕዝብ ድምፅ ዝርፊያና በፖለቲካ አፈና ገፅታው ብቻ አጥሮ ሕዝባችንን ያልበላው ቦታ በሚያኩ "የደፈና" መፈክሮች የተቃኘ ስትራቴጂ ነው፡፡

ከአለፈው ሂደት ትምህርት ቀስመናል፣ የዛሬውን ተጨባጭ ሁኔታና ቀጣዩን የጥፋት

ሂደት በትክክል አጢነናል ካልን ሕዝባችንን ከጨለምተኝነትና ከትጥቅ መፍታት አባዜ አላቅቀን መልሰን የትግሉ ማዕከልና ባለቤት የምናደርገው ምን ክቡርና አገራዊ ቢሆኑም ትላንት ሕዝባችንን በሚሊዮን እያስቆጠሩ ከዳር-እስከ-ዳር ባንቀሳቀሱት የፖለቲካ መፈክሮች ብቻ ሊሆን አይችልም። ዛሬ ሕዝባችን በተቸባጭ እየተሰቃየባቸው ያሉትን የቅልበሳው የኢኮኖሚና የማኅበራዊ መዘዞች "ነገ ወያኔ ወድቆ ዴሞክራሲ ሲሰፍን እንያያዛቸዋለን" በሚል ፈሊጥ ችላ ብለን የትግላችን አድማስ በዴሞክራሲ፣ በሕግ የበላይነት፣ በሲቪክና የሙያ ማኅበራት ግንባታ ጥያቄዎች አጥረን እንንቀሳቀሳለን ካልን በነዚህ ዛሬ ባለው ተጨባጭ ሁኔታ "ከሰማይ የራቁ" መፈክሮችና በዚኽ አካሄድ ሕዝባችንን መልሰን የትግሉ ማዕከልና ባለቤት እናደርጋለን ማለት ትላንት በፀረ-ደርግ ትግሉ ዘመን እንዳልሠራ የታየውን አካሄድ ዛሬ መልሶ መድገም ይሆናል ብለን እንሰጋለን።

እርግጥ ዴሞክራሲ፣ የሕግ የበላይነት፣ የዳኝነት ነፃነት፣ ወዘተ.. ተጠያቂነት ባልሰፈነበት ሁኔታ ለእነዚህ የሕዝባችንን ተጨባጭ የኀልውና ችግሮች ዘላቂ መፍትኄ ልናገኝላቸው እንደማንችል ግልጽ ነው። የዚያኑ ያኽል ደግሞ ሁለት ግልጽ የሆኑ ቁም-ነገሮች አሉ።

አንደኛ ሕዝባችን ከዳር-እስከ-ዳር ተነስቶ በአንድ አቅጣጫ እስካልተንቀሳቀሰ ድረስ እነዚህ እሴቶች እውን የሚሆኑበት ምንም ተአምር አይኖርም።

ሁለተኛ ለአገራችን ነፃነት ወሳኝ የሆነው ሕዝባዊ እንቅስቃሴ እውን ይሁን ከተባለ በአገራችን ባለው ተቸባጭ ሁኔታ የማይነጣጠሉ ነገሮችን ነጣጥሎ ዛሬ በዴሞክራሲ፣ በሕግ የበላይነት፣ በተኡማት ግንባታና "በወያኔ መወገድ" ላይ አተኩረን የሕዝባችንን ጉረሮ አንቀው የያዙትን የኀልውና ችግሮች ነገ እንያያዛቸዋለን ማለት ወንዝ የማያሻግር አካሄድ ነው።

ኅብረታችን "ትኩረት ለሕዝባችን ተጨባጭ ችግሮች" ብሎ ጥሪ ሲያስተጋባ የማይነጣጠሉ ነገሮች አይነጣጠሉ "ዛሬውኑ ለኅልውናህና ለመብትህ ታገል" በሚል ጥሪ ሕዝባችን የትግሉ ማዕከልና ባለቤት ሊሆን የሚችልበትን ዘዴ ለመጠቆም እንጂ የፖለቲካው ትግል ወደ ጎን ይተው ለማለት እንዳይደለ ግልፅ ነው። በዚኽ ጉዳይ ላይ ያለንን እይታ ቀደም ሲል "ሰላማዊ ሕዝባዊ ትግል ስንል" በሚል ርዕስ ባወጣነው መግለጫ ላይ እንዳልነው፤ "ኅብረታችን ሕዝባዊ ሰላማዊ ትግል ሲል አንደኛ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ብሶታቸውን አንግበው ለችግራቸው መፍትኄ ለመሻት እንዲታገሉ መቀስቀስ ያስፈልጋል ማለቱ ነው። ሁለተኛ እነዚኽ የተለያዩ የኅብረተሰብ ክፍሎች ተራ በተራ መነሳታቸው ተራ በተራ ከመመታት የማያልፍ አጉል መስዋዕትነት እንዳይሆን ሁሉም "ብሶትህ ብሶቴ" በሚል መንፈስ በትግግዝና በአንድነት እንዲነሱ ሁኔታዎችን ማመቻቸት ያስፈልጋል ማለት ነው። ሦስተኛ በዚኽ መልክ የሚንቀሳቀሱት የኅብረተሰብ ክፍሎች ዛሬ የሚገኙበት ከባድ ቀውስ የግንቦት ቅልበሳ መዘዝ እንደሆነ እንዲገነዘቡና ማንኛውም ዘላቂነት ያለው መፍትኄ ከኢሕአዴግ መንግሥት ከሥልጣን መወገድና ዴሞክራሲ በሰፈነበት ሁኔታ በሕዝብ ፊት ተጠያቂ የሆነ መንግሥት መመሥረት እንደሆነ አውቀው እዚያው በዚያው ለዴሞክራሲ ሥርዓት እንዲታገሉ መቀስቀስ ያስፈልጋል።"

የግንቦት ድሎች ዋና ባለቤት የሆኑትን ሚሊዮኖች በእንደዚህ ዓይነቱ ስትራቴጂ መልሰው የትግሉ ባለቤትና ማዕከል እንዲሆኑ ካልሠራን የሕዝባችን ወደ ጠርዝ መገፋትና ከትግሉ መድረክ መገለል የግድ የግንቦት እሴቶችን መክሰምና የነዚኽ አራማጅ የነበሩት ግንባር ቀደም ኃይሎችም ከመድረኩ መገለልን እንደሚያስከትል ጠንቅቀን መገንዘብ ይኖርብናል። ይኽ ማለት ግን ትግሉ ቆመ ወይም ይቆማል ማለት አይደለም። እኛንም ሆነ የኢትዮጵያን ሰፊ ሕዝብ በማያካትት መልኩ አገራችን ከግንቦት እሴቶች ጋር እምብዛም

*ግንኙነት በሌላቸው እንዲያውም እነዚኽን እሴቶች በሚፃረሩ አጀንዳዎች ዙሪያ የመድማትና የመድቀቅ አደጋ ይከሰታል ማለት ነው፡፡ ይኽ ደግሞ ወደ ሦስተኛው የደፈና ስምምነት ነጥብ ያመጣናል፡፡*

*ዛሬ ዴሞክራቶች አካባቢ ሁሉም የሚስማማበት ሌላ ቁም-ነገር ቢኖር የኢሕአዴግ አገዛዝ በሥልጣን ላይ ከቀጠለ የአገራችን ሰላም፣ አንድነትና ኅልውና ሁኔታ ከባድ አደጋ ላይ ሊወድቅ የሚችልበት ሁኔታ አለ የሚለው ነጥብ ነው፡፡ ያለንበት ሁኔታ በአንድ በኩል ለኤርትራ መገንጠል ከሸዓብያ ይበልጥ አስተዋጽዖ አድርጌአለሁ በሌላ በኩል ደግሞ እኔ ከሥልጣን ከተወገድሁ አገሪቱ እንደ አገር መቀጠል አትችልም የሚል አስገንጣይ/ ተገንጣይ ኃይል በመንግሥትነት ደረጃ የተቀመጠበት በሌላ በኩል ደግሞ የአንድነት ኃይሎች ከነክፍፍላቸውና ከነድክመታቸው በተቃዋሚነት ደረጃ የሚንቀሳቀሱበት አስገራሚ፣ እጅግ አደገኛና በታሪካችን ታይቶ የማይታወቅ ሁኔታ ነው፡፡ የግንቦት ድሎች አንድ የማይናቅ ገፅታ ይኽ የጥፋት ኃይል በሚቆጣጠረው የመንግሥት ንዋይና ንብረት፣ ሠራዊት፣ ፖሊስና የፀጥታ ክፍልን ያጠቃለለ ድርጅታዊ አቅም እየታገዘ ሲያራምድ የቆየውን አንዱን የሕዝብ ወገን ከሌላው፣ ሐይማኖትን ከሐይማኖት የማናከስ ሂደት ሕዝባችን እንደ አንድ ሰው ተነስቶ በመቃወሙ የሕዝብ ወንድማማችነትና የአገር አንድነት እሴቶች በድል አድራጊነት መውጣታቸው ነበር፡፡ የግንቦት ቅልበሳ ማለት የነዚኽ በጎ ግኝቶችና እሴቶች መቀልበስ ማለት ነው፡፡*

*በመሆኑም ዛሬ ግንቦት ላይ ከስመው የነበሩት የሐይማኖትና የብሔረሰብ ግጭቶች እንደገና ብቅ ብቅ እያሉና በኢሕአዴግ ስውር ደባ እየታገዙ አገራችንን ወደ ጥፋት ይዘው የሚነጉዱበት ሁኔታ እየተፈጠረ ነው፡፡ የኢትዮጵያ ዴሞክራቶችና አገር-ወዳድ ኃይሎች የግንቦት የሕዝብ ድሎች ለማስመለስ ብለን የምናደርገው ትግል ግቡን እንዲመታ ከፈለግን እንደ ፖለቲካ አፈናው፣ እነደ ኤኮኖሚውና ማኅበራዊ ቀውሶቹ ይኽም አንዱ የሕዝብ ክፍል በሌላው ላይ፣ ሐይማኖት በሐይማኖት ላይ እንዳይነሣ በአንድ ድምፅ መቀስቀስ ይኖርብናል፡፡*

*ይኽንን ከማድረግ ይልቅ በአንዳንድ አካባቢዎች "ዛሬ ዋናው ትግል ወያኔን የማስወገድ ትግል ነው" በሚል ፈሊጥ ይኽንን የሕዝብ ወንድማምችነትና የአገር አንድነት ጥያቄም ልክ እንደ ኤኮኖሚውና የማኅበራዊ ቀውሶች "ነገ ዴሞክራሲ ሲሰፍን እንፈታዋለን" በሚል ስሊት በይደር አስቀምጠው የግንቦትን ቀልባሾች በመዋጋት ስም የግንቦትን እሴቶች እውንነት ከማያምኑና "የኛ" ብለው ከማይቀበሉ ኃይሎች ጋር የትግል አንድነት የመጥራት አካሄዶች ይታያሉ፡፡ ዛሬ የከሰሙና ኅብረቱም ከአገራዊና ሕዝባዊ መተክሉና ከግንቦት እሴቶች አኳያ ተቃውሞት የነበረው "ትብብር ለነፃነትና ለዴሞክራሲ"* (AFD) *የተባለው ስብስብ የእንደዚኽ ዓይነቱ ስሌት ውጤት ነበር፡፡ አሁንም ቢሆን በግንቦት እሴቶች ዙሪያ የሚሊዮኖችን እንደገና መቀስቀስ ስንችልና ሲገባን በዚኽ በኩል የገጠመንን ችግር "ለማካሰስ" በእነዚኽ እሴቶች ዙሪያ የማይንቀሳቀሱ ኃይሎች ጋር "ፀረ-ወያኔ ትግል" የመሰለፍ አዝማሚያ እየታየ ነው፡፡ ይኽ አካሄድ ከቀጠለ ግንቦት ልይ የትግልም የአገራችንም እጣ-ፈንታ ባለቤት የነበሩት ሚሊዮኖችና የዚኽ ተጋድሎ ግንባር-ቀደም የነበሩ ታጋይ ኃይሎች ወደ ዳር ተገፍተውና ተበትነው ትላንት "የት ነበሩ?" የሚባሉ ተቃዋሚዎችና ለአገራችን በጎ የማያስቡ ባዕዳን መኻል መድረኩን የሚቆጣጠሩበትና ሕዝባችንን የሚያደሙበትን፣ አገራችንንም የሚያደቁበትን ሁኔታ በማመቻቸት ላይ እንደሆንን መገንዘብ ይኖርብናል፡፡*

*እንግዲህ ከዚኽ ሁሉ አስቸጋሪ ሁኔታ ለመውጣትና የግንቦት እሴቶችን እውን ለማድረግ ምን መሠራት አለበት የሚለው ጥያቄ ይነሣል፡፡ የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት ዛሬ ላለንበት ውጥንቅጡ ለወጣ ሁኔታ ይኽ ነው ብሎ የሚሰነዝረው ቀላል መፍትኄ*

የለውም፡፡ ከዚኽ በፊት ተብሎ ተብሎ ያላለቀለት አዲስ የሚለው ነገርም የለውም፡፡ ከፍ ብለን እንደጠቀስነው ቅልበሳው አሳሳቢ ነው፣ ሕዝባዊ ትግል የኢሕአዴግ ፀረ-ሕዝብና ፀረ-ኢትዮጵያ አቋም አራማጅ መንግሥት ካልተወገደና ቅልበሳው ሕዝብን ማዕከል ባደረገ የተባበረ ትግል ካልተቀለበሰ አገራችን ወደ ጥፋት እየሄደች እንደሆነ ሁላችንም እንስማማለን፡፡ ሁላችንም ለዚች አገራችንና ለዚኽ ሰማዕት ሕዝባችን ያለንን በጎና የጋራ የሆነ ራእይ እውን ለማድረግ እንመኛለንና ከነዚኽ አጠቃላይ ስምምነቶች ዘልቀን በመምከር ከአለንበት አስቸጋሪ ሁኔታ የሚያወጣን የጋራ ስትራቴጂ መንደፍ ይኖርብናል፡፡ በዚኽ ምድር ካሉ ቀውሶች ከተገቢ ድርሻዋ በላይ የተሸከመች አገራችን በአንፃሩም ለእናት አገርና ለሕዝብ ጥቅሞች መከበር ሲባል የተፈለገውን መስዋዕትነት ለመክፈል የመውጫ በር የማይከጅሉና ወደ ኬላ በማይሉ አገር-ወዳድና ወገን-አፍቃሪ ታጋይ ዜጎች የተትረፈረፈች አገር ናት፡፡ በመሆኑም ምን ያኽል ፈተና ቢያጋጥማቸው ከዚኽ የአገር ፍቅራቸው በሚመጥን ጥራት ሁኔታዎችን ተንትነው በጋራ ስትራቴጂ ለመራመድ ከተነሱ ከኢሕአዴግ የጥፋት ኃይሎች ባሻገር ይኽችን አገር ከአኩሪ ታሪኳ የሚመጥን ብሩኅ የሆነ የወደፊት ተስፋ እንዲኖራት ማድረግ አያቅታቸውም ከሚል እምነት በመነሣት አፋችንን ሞልተን “አዎን ይቻላል፣ መቻልም ይኖርበታል” እንላለን፡፡

እስካሁን ካገኘነው ልምድ ከተነሣንና ከሦስት አራት ዓመታት በፊት ጀምሮ ሁሉም የትግል አንድነት እያለ ጥሪ ሲያስተጋባ፣ ይኽንን እውን ለማድረግ ሁሉን-አቀፍ ጉባዔ የሚል አሳብ ሲያቀርብ፣ ይኽንን ለማመቻቸት ደግሞ “አስቸኳይ ጥሪ” እያስተጋባ ያደረግነው ጉዞ በዳተኝነት ተውጦ ምንም ፍሬ ሳይሰጥ ቀርቷል፡፡ ዛሬም ቢሆን ከዚኽ የተለየ ጥሪ አይኖረንም፡፡ የግንቦት ኃይሎች በአስቸኳይ የጋራ ጉባዔ አዘጋጅተው መጀመሪያ በመበተንና ትጥቅ መፍታት ላይ ያለው ግንባር-ቀደም ኃይል መልሶ የሚሰባሰብበት፣ ከዚያም ይኽ ግንባር-ቀደም ኃይል ጥራትና ተጨባጭነት ባለው የትግል አጀንዳ የኢትዮጵያ ሕዝብ መልሶ የትግሉ ባለቤትና ማዕከል የሚሆንበትን ስትራቴጂ መንደፍ ይኖርበታል፣ ይኖርብናል፡፡ በዚኽ ሁሉም የተስማማበት ሆኖም ግን እስካሁን ሁነኛ ባለቤት አጥቶ ሲጉላላ በቆየ የጋራ ጉባዔና የጋራ ስትራቴጂ ጉዳይ የታየውን ዳተኝነት ስንታዘብ “ይቻላል” በሚለው ብሩኅ ተስፈኛ መፈክር መወሰን አንችልም፡፡ ከዚኽ ይልቅ ከጊዜ ጋር ችግሮቻችን ሁሉ እየከፉና እየተወሳሰቡ እንደሚሄዱ፣ ከጊዜ ጋር ከእኛም ከሕዝባችንም ቁጥጥር ውጭ የሆነና ውጥንቅጡ የወጣ ሁኔታ ሊከሰት እንደሚችል ስለምንጠብቅ ከዚኽ መፈክር አልፈን የአገር ኅልውና ጉዳይ ነውና “**መቻል አለበት**! **መቻልም ይኖርበታል**!” ብለን በመነሣት ይኽ እምነት በሚሰጠው የአልሞት-ባይ-ተጋዳይ የመንፈስ ጥንካሬና ጥናት ወቅቱ በሚጠይቀው ፍጥነት ለመራመድ ዝግጁ መሆን ይኖርብናል፡፡

የኢትዮጵያ ዴሞክራሲያዊ ኃይሎች ኅብረት (ኢዴኃኅ)

ግንቦት ፯ ቀን ፪ ፩ ዓ/ም (May 15, 2009)